
# ከታሪክ ማሕደር

## ወሎ የሚለው ስም ከየት እንደመጣ ስንቶቻችን እናውቃለን?

ታአሪክ እንደሚአስተምረን በአስራስድስተኛው ክፍለ ዘመን መሃል አገር ያለው ሕዝብ በግራኝ ጦርነት ከተዳከመ በኃላ የኦሮሞ መስፋፋት ሲጀመር ለቱ ለማ የሚባለው የኦሮሞ ጎሳ ሸዋን ሲቆጣጠር ሌሎቹ የኦሮሞ ጎሳወች በተለያዪ አቅጣጫ ተከፋፍለው ሌላውን አካባቢ ለመውረር ሄዱ፡፡ አንጎት ተብሎ ይጠራ የነበረውን አካባቢ የወረረው ወሎ የሚባለው የኦሮሞ ጎሳ ስለነበር አንጎትን ወሎ ብሎ ስሙን ቀዪረው ይባላል፡፡ ታዲያ ታሪካችን ይህን ጭምር የሚአጠቃልል ከሆነ ሁሉንም **ኬኛ ኬኛ** ከማለትና በሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን እየኖረን እንዳአስራስድስተኛው ክፍለ ዘመን ከማስብ በጋራ ሆነን ድህነትን በመዋጋት ማደግ አይሻልምን?

አንዳንድ የኦሮሞ ጽንፈኞች የኢትዮጲያ ታሪክ የመቶ አመት ብቻ አስመስለው ሊአቀርቡ ቢፈልጉም እውነቱ ግን ከዛ የራቀ ነው፡፡ ለምሳሌ የፋይናንስ እና የውጭ ጉዳይ ምኒስቴር ከዛም በተጨማሪ በተለያዪ ሃላፊነት ላይ ሆነው አገራቸውን ያገለገሉት የተከበሩ አቶ ይልማ ደሬሳ **የእኢትዮጲያ ታሪክ በአስራስድስተኛው ክፍለ ዘመን** በሚለው መጻህፋቸው እንዲህ ሲሉ ይገልጽታል፡፡


፪፻፵፬ የኢትዮጵያ ፡ ታሪክ ። 244

### ስለ ፡ ወሎ ፡ ጎሣ ፡ መሰደድ ።

በዘመናችን ፡ የሸዋ ፡ [illegible] ፡ ምድር ፡ የሚባለውን ፡ አገር ፡ በዕጣ ፡ ለቱለማ ፡ ጎሣ ፡ ለቀውለት ፡ የሄዱትን ፡ የሌሎችን ፡ ጎሣዎች ፡ ታሪክ ፡ ከመፈጸም ፡ አስቀድሞ ፡ የወሎን ፡ ጎሣ ፡ ታሪክ ፡ በአጭሩ ፡ እናስረዳለን ። ከአፍ ፡ ታሪክ ፡ እንደምንሰማ ፡ የወሎ ፡ ጎሣ ፡ ከቱለማዎች ፡ የተለያየው ፡ መጫዎች ፡ አዋሽን ፡ ተሻግረው ፡ ወደ ፡ መዕራብ ፡ ከተጓዙ ፡ በኋላ ፡ ነው። በ፲፭፻፶፬ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በገዳ ፡ ሮበሌ ፡ የጀመረው ፡ የአምስቱ ፡ ገዳ ፡ ዙሪያ ፡ ተፈጸመ። በዚሁ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት፡ ቡታ ፡ አርደው፡ የነገዱን ፡ የአስተዳደር ፡ ሥልጣን ፡ የተረከቡት ፡ ሉባዎች ፡ ገዳቸውን ፡ ሐንፋፋ ፡ ወይም ፡ ዱሉ ፡ ብለው ፡ ሰየሙት ። እነዚህ ፡ ሉባዎች ፡ የሚልባ ፡ ባለገዳ ፡ ልጆች ፡ ስለ ፡ ሆኑ ፡ እንደ ፡ ደንቡ ፡ ገዳቸው ፡ ሚልባ ፡ ሊባል ፡ ይገባ ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ኦሮሞዎች ፡ ከወላቡ ፡ ተንቀሳቅሰው ፡ ሰፊ ፡ ምድር ፡ ለመያዝ ፡ ከተለያዩ ፡ በኋላ፡ አንድ ፡ አንድ ፡ ጎሣዎች ፡ የገዳዎችን ፡ ስም ፡ እንደ፡ለወጠው ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ተገልጾዋል። ይሁንና ፡ የወሎን ፡ ነገድ ፡ ዘመቻ ፡ ለመጀመሪያው ፡ ጊዜ ፡ የመሩት ፡ የሐንፋፋ ፡ ወይም ፡ የዱሉ ፡ ባለገዳዎች ፡ ናቸው ። ታላቁ ፡ ወረራ ፡ ከመጀመሩ ፡ አስቀድሞ ፡ ወላቡንና ፡ ቱሉ ፡ አምዱልን ፡ የጋሎች ፡ መነሾ ፡ ቦታ ፡ አድርገን ፡ ስለ ፡ ቈጠርን ፤ የወሎ ፡ ጎሣ ፡ ከመንቀሳቀሱ ፡ አስቀድሞ ፡ መካከለኛውን ፡ ደጋ ፡ ቱለማዎች ፡ በምሥራቁ ፤ ደጋ ፡ ቱለማዎች ፡ በምዕራብ ፡ ደጋ ፡ መጫዎች ፡ ሰፍረውበት ፡ እናገኛለን ። አራተኛው ፡ ነገድ ፡ ለሆነው ፡ ለወሎ ፡ ጎሣ ፡ የቀረው ፡ ክፍያ ፡ ከሰሜኑ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ደጋ ፡ መሻማት ፡ ብቻ ፡ ነበር ። ስለዚህ ፡ ይህ ፡ ጎሣ ፡ ወደ፡ሰሜን ፡ የሚጓዝበትን ፡ መንገድ ፡ ማግኘት ፡ ነበረበት ። ይልቁንም ፡ በነዚህ ፡ አውራጃዎች ፡ ውስጥ ፡ የደረጀ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ጦር ፡ ስለሚገኝባቸው ፡ እነሱን ፡ አቋርጦ ፡ ማለፍ ፡ የማይቻል ፡ ነበር ። የሆነው ፡ ሆኖ ፡ የሐንፋፋ ፡ ገዳ ፡ መሪዎች ፡ ከአዳ ፡ ነቤ፡ ተነሥተው ፡ መጀመሪያ ፡ ወደ ፡ ምሥራቅ ፡ ከተጓዙ ፡ በኋላ ፤ በደጋውና ፡ በቆላው ፡ መካከል ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ በሚተዳደሩ ፡ ወረዳዎችና ፡ በአዳሎች ፡ ድንበር ፡ ላይ ፡ አልፈው ፡ ወደ ፡ ሰሜን ፡ ለማቃናት ፡ መደቡ ። የወሎ ፡ ክፍል ፡ ጎሣዎች ፡ በጉዞአቸው ፡ ጊዜ ፡ አዋሽን፡ ተሻግረው ፡ ከቲሲኖ ፡ ከምትባል ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ኃያሌ ፡ የተባ

245 የኢትዮጵያ ፡ ታሪክ ። ፪፻፵፭

ለው ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ጦር ፡ መንገዳቸውን ፡ ለመዝጋት ፡ ሰፍሮ ፡ አገኙት ። ከቲሲኖ ፡ ላይ ፡ ከዚህ ፡ ከንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ኀይለኛ ፡ ሠራዊት ፡ ጋራ ፡ ታላቅ ፡ ውጊያ ፡ አደረጉ ። በዚህ ፡ ዘመን ፡ የወሎም ፡ ጎሣዎች ፡ እንደ ፡ ወንድሞቻቸው ፡ እንደ ፡ ቱለማና ፡ እንደ ፡ መጫዎች ፡ የደረጀ ፡ ፈረሰኛ ፡ ስለ ፡ ነበራቸው ፡ ጊዮርጊስ ፡ ኃያሌን ፡ አሸንፈው ፡ መንገድ ፡ ማስለቀቅ ፡ ቻሉ ።

ካቲሲኖ ፡ ላይ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ኃያሌን ፡ ድል ፡ ካደረጉ ፡ በኋላ ፤ የደጋውን ፡ አፋፍ ፡ ተከትለው ፡ ጉዞአቸውን ፡ ወደ ፡ ሰሜን ፡ ከቀጠሉ ፡ በኋላ፡ ከዚያም ፡ ወጥተው ፡ በአንጎት ፡ አውራጃ ፡ አፋፍ ፡ ደጋውን ፡ አገር ፡ ያዙት ፡ ከጐሳው ፡ መካከል ፡ ተከፍሎ ፡ በአንጎት ፡ በስተ ፡ ደቡብ ፡ ያለውን፡ አገር ፡ ይዞ ፡ ወሎ ፡ ብለው ፡ ሰየመው ። ሌሎችም ፡ ዛሬ ፡ የጁ ፡ የሚባለውን ፡ ወረዳ፡ ከያዙ፡ በኋላ ፤ ወደ፡ሰሜን ፡ ቀጥለው፡ ያዘቦና፡ የራያ ፡ ጎሣ ፡ ዛሬ ፡ የሚኖርበትን ፡ አውራጃ ፡ ይዘው ፡ ሰፈሩበት ። እነዚህን ፡ አገሮች ፡ ይዘው ፡ ከሰፈሩበት ፡ በኋላ ፡ የሐንፋፋ ፡ ባለገዳዎች ፡ ጋንገዝንና ፡ ሳይንትን ፡ መውረር ፡ ጀመሩ ። ከነዚህም ፡ አንዱ ፡ ባርቱማ ፡ የተባለው ፡ ጎሣ ፡ ዋቃ ፡ የተባለውን ፡ የሐርቦን ፡ ወንድም፡ ወግቶ ፡ ከገደለው፡ በኋላ ፡ በጌምድርን ፡ ወርሮ ፡ ከመካከለኛው ፡ ያማራ ፡ አገር ፡ ጦር ፡ ከተዋጋ ፡ በኋላ ፤ ወደ ፡ ፊት ፡ መግፋት ፡ ተስኖት ፡ ከዚያው ፡ መቆም ፡ ግዴታ ፡ ሆነበት ።

እንግዲህ ፡ የወሎን ፡ ጎሣ ፡ በ፲፮ኛው ፡ መቶ ፡ መጨረሻ ፡ አማራና ፡ ትግሬ ፡ ድንበር ፡ ላይ ፡ እንተዋቸውና ፡ ቀጥለን ፡ የቱለማ ፡ ጎሣ ፡ ከአዳ፡ ነቤ ፡ በተንቃነቀ ፡ ጊዜ ፤ ወደ ፡ አደረገው ፡ ዘመቻ ፡ እንመለስ ።

በ፲፭፻፷፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የሐንፋፋ ፡ ገዳ ፡ ፰ ፡ ዓመት ፡ ተፈጽሞ ፡ ከአርባ ፡ ዓመት ፡ በፊት ፡ በሙዳና ፡ ገዳ ፡ ጊዜ ፡ ቡታ ፡ ያረደው ፡ ትውልድ ፡ ልጆች ፡ ባለገዳ ፡ ለመሆን፡ ደረሱ ። ቡታ ፡ ባረዱም፡ ጊዜ ፡ ገዳውን፡ ሮበሌ፡ ብለው ፡ ሰየሙት ። በዚህ ፡ በሮበሌ ፡ ገዳ ፡ ጊዜ ፡ ትልቅ ፡ ዘመቻ ፡ ያደረገው ፡ የቱለማ ፡ ጎሣ ፡ ነው ፤ እላይ ፡ እንደተመለከተው ፡ ሁሉ ፡ ከረዩዎች ፡ ወደ ፡ ምሥራቅ ፡ መጫዎች ፡ ወደ ፡ ምዕራብ ፡ ወሎዎች ፡ ወደ ፡ ምሥራቅ ፡ ሰሜን ፡ መጓዛቸውን ፡ ስናትት ፡ ቱለማዎችን ፡ አዳ ፡ ነቤ ፡ ላይ ፡ ተውናቸው ። በ፲፭፻፷፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ቱለማዎቹ ፡ ከአዳ ፡ ነቤ ፡ ዙሪያ ፡ ተን

ታሪክን የማነሳው ለመወቃቀስ ሳይሆን የተጎጂ ትርክት ፈጥረው አሁን ጊዜ አገኘን የሚሉ የኦሮሞ ጽንፈኞች ሕዝቡን የሚያሰቃዩትና የኦሮሙማን ፐሮጀክት ለማሳካት የሚያደርጉት እሩጫ ተገቢ እንዳልሆነና ሁላችንም አብረን በሰላም

የምንኖርብትን ስርአት ካልፈጠርን አሁን የሚአደርጉት ዘላቂ ሳዩሆን ጊዜያዊ መሆኑን ሊረዱት ይገባል ለማለት ነው፡፡ በተጨማሪም የኦሮሞ ሕዝብም ሆነ ሌላው ኢትዮጲያዊ ታሪካችንን እና አሁን የደረስንበትን በትክክል ብናውቅ ጥሩውም መጥፎውም ታሪካችን የሁላችንም መሆኑን ለመረዳት ይጠቅማል በማለት ነው፡፡ ሕዝበአችን አንድ የሚያረገው ብዙ እሴቶች ያሉት በመሆኑ አሁን በምናዩው የውሸት ትርክት በመከፋፈል አደጋ ላይ መውደቅ የለበትም፡፡ ጥያቄው መሆን ያለበት አሁን ካለንበት ተነስትን እንደ አገርም እንደሕዝብም እንዴት መቀጠል አለብን ነው እንጂ እንዴት ወደኋላ እንንተት ሊሆን አይገባም፡ በጽሞና ካዪነው ባለንበት በዚህ በሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን ለማደግ እና ድህነትንም ለማሸነፍ እንደ አገር እና እንደ ሕዝብ በአንድ ላይ ከመቆም ሌላ የተሻለ አማራጭ የለንም፡፡

## አሁን ከሚካሄደው የኦሮሙማ ፕሮጀክት ተጠቃሚው ማነው?

አዲስ አበባ ላይም ሆነ፤ ሸገር ከተማ ለመስራት ባፈረሱት የድሆች መኖሪያ ቤቶችእና የእምነት ተቋማት፤ ተጠቃሚው በኦሮሞ ሕዝብ የሚነግድ ጽንፈኞች ብቻ ናቸው፡ በየጊዜውም ከሚያፈናቀሉት፤ ከሚያፍኑትና ከሚገደሉት ሕዝብ ባአጠቃላይ አሁን እየተገበረ ባለው የኦሮሙማ ፕሮጀት ከኦሮሞ ጽንፈኞች ገዚአዊ ጥቅም በስተቀር ሌላው የህብረተሰብ ክፍል የኦሮሞ ሕዝብንም ጨምሮ ተጎጂ እንጂ ተጠቃሚ አይደለም፡፡ ስለዚህ የኦሮሞ ሕዝብም ሆነ ሌላው ሰላምና እድገት የሚፍለግ ኢትዮጲያዊ ሁሉ በአንድነት በመቆም ይህን የጽንፈኞች ቡድን በቃ ሊለው ይገባል፡፡

እሬሳ በአደባባይ ተጎትቶ ሲሰቀል ድምጻችንን ከፍ አርገን ሁላችንም ለፍትሕ ቆመን ቢሆንና መንግስትን ተጠያቂ አርገን ቢሆን አሁን የደረስንበት ባልደርስን ነበር፡፡ አሁንም የኦሮሙማን ፕሮጀክት መታገል አማራጭ የሌለው የህልውና ጉዳይ በመሆኑና ለኦሮሞውም፤ ለአማራውም፤ ለጉራጌውም፤ ለትግሬውም፤ ለሁሉም ኢትዩጲያዊ በሙሉ የሚአዋጣ ስላልሆነ ተባብረን ልናስቆመው ይገባል፡፡ ይህ ካልሆነ ግን መጭው ጊዜ አስፈሪ እና አሳዛኝ መሆኑን ከወዲሁ ሁላችንም ልንገነዘብ ይገባል፡፡

ካክብሮት ጋር
ሺመልስ